# <u>የአንድነት ፓርቲ አባላት እርስ በርስ ተደባደቡ!</u>
# ፓርቲው ከቀውስ ወደ ቀውስ የሚያደርገው ጉዞ ቀጥሏል

በምርጫ 97 ዋዜማ ተቋቁሞ የነበረው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ (CUD) ከፈረሰና አመራሩ ታስረው ከተፈቱ በኋላ በወ/ሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ ግንባር ቀደም ሚና የተቋቋመው አንድነት ለፍትህና ለዴሚክራሲ ፓርቲ (UDJ)፤ ከተቋቋመበት ዕለት ጀምሮ የፖለቲካ ሥራ በመስራት ሕዝብን ከማደራጀት ይልቅ በውስጥ ችግሩ ተጠፍሮ ከቀውስ ወደ ቀውስ እየተሸጋገረ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን መረጃ አመለከተ።

የአንድነት ፓርቲ ቀውስ የጀመረው የፓርቲው የምስረታ ሂደት በመከናወን ላይ በነበረበት ወቅት እንደነበር የዜና ምንጫችን አስታውሶ፣ "ገና ፓርቲው ሳይመሰረት አንዳንድ መስራች አባላቱ በፓርቲው ውስጥ በሚኖራቸው ስልጣንና ኃላፊነት ዙሪያ የሚዶልት የየራሳቸውን ቡድን አደራጅተው ይሻኮቱ ነበር" ብሏል።

በምስረታው ሂደት የታየው ችግርና ቡድናዊ እንቅስቃሴ ተፈትሾ እልባት ሳይበጅለት ፓርቲው ተመስርቶ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ በሊቀ መንበርነት መመረጧንና ከዚያ ጊዜ በኋላ የፓርቲው እንቅስቃሴ በሰከነና በረጋ አኳኋን ይመራል የሚል ተስፋ ፈንጥቆ እንደነበር የዜና ምንጩ ጠቅሶ፤ ይሁን እንጂ፣ ፓርቲው መሰረታዊ ችግሮቹን ፈትሾ መፍትሄ ማስቀመጥ ባለመቻሉ እያንዳንዱ እርምጃው ከችግር ወደ ችግር የተረማመደ መሆኑንና ይህም ሁኔታ ሊቀ መንበሯን ጭምር እያሳሰባቸው በመምጣቱ "እኔ ጄኔራል ሆኜ እየመራሁ ዘወር ብዬ ሳያቸው አጠገቤ የሉም" የሚል የምሬት ስሜታቸውን ከመታሰራቸው በፊት ለአንድ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ ምልልስ መግለጻቸውን ከዜና ምንጩ ያገኘነው መረጃ አብራርቷል።

ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ እንደገና ከታሰሩ በኋላ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ታፍኖ የተያዘውና ውስጥ ውስጡን ሲግፈጠፈጥ የነበረው ችግር ጊዜ ጠብቆ መፈንዳቱንና በፕሮፌሰር መስፍን የሚመራ "የአንድነት መርህ ይከበር" የሚል ቡድን እስከ መፍጠር ደርሷል ይላል የዜና ምንጩ የላከው መረጃ። መረጃው አያይዞም፤ "'የቅንጅት ህጋዊ ወራሽ ነኝ' የሚል አቋም ይዞ የተመሰረተውና የሀገሪቱን ችግር እቀርፋለሁ የሚለው አንድነት ፓርቲ በውስጡ የገጠመውን ችግር በዴሞክራሲያዊ አግባብ ለመፍታት ባለመቻሉ የእነ ፕሮፌሰር መስፍን ቡድን ግዘፍ ነስቶ አደባባይ በመውጣት የፓርቲውን ገመና ይፋ በማድረግ የአንድነትን ከቀውስ ወደ ቀውስ መሸጋገር ይበልጥ አረጋገጠ" ይላል።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ፓርቲው በያዘው ዕቅድ መሰረት ጽ/ቤት መክፈቱንና ሕዝብ ማደራጀቱን እርግፍ አድርጎ ትቶ እዚህም እዚያም የተለኮሱ እሳቶችን በማዳፈን ለውስጣዊ ችግሮቹ ጊዜአዊ መፍትሄ ለመስጠት ኮሚቴ ሲያቋቁምና መግለጫ ሲሰጥ መባጀቱን የመረጃ ምንጫችን ገልጿል።

አንድነት ፓርቲ "መድረክ" የተሰኘው የፓርቲዎች ስብስብ አባል ለመሆን የወሰደው ውሳኔ የፓርቲውን ችግር ለማባባስ እንደ ቤንዚን ሆኖ ማገልገሉን መረጃው አመልክቶ፣ ፕሮፌሰር መስፍንን እና የፓርቲውን ላዕላይ ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶ/ር ሽመልስ ተ/ጻዲቅን ጨምሮ "የአንድነት መርህ ይከበር" የሚሉ በተለያ የፓርቲው

መዋቅር የሚገኙ አባላትን ማባረሩ ደግሞ የፓርቲውን ችግር በማጋጋም የቀውሱን መባባስ ፏሪና ቀጣይ አድርጓል ሲል አብራርቷል፡፡

አንድነት ፓርቲ እና “የአንድነት መርህ ይከበር” ባዩ ቡድን ከፍጥጫ፣ ከመግለጫና ከጽሁፍ እሰጥ አገባ ወደ ኃይል እርምጃ የተሸጋገሩት ደግሞ ፓርቲው ባባረራቸው የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ምትክ የማሟያ ምርጫ ለማካሄድ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በጠራበት ዕለት ነበር፡፡ በዚህ ዕለት በሁለቱ ባላንጣ ቡድኖች መካከል የታየው ፍጥጫ ለፓርቲው ቀጣይ ቀውስ ማቀጣጠያ የሚሆኑ ምቹ ሆኔታዎችን ፈጥሮ ማለፉን መረጃው አመልክቶ፣ ዕሑድ ህዳር 27 ቀን 2002 ዓ.ም የተከሰተውን ኃይል የቀላቀለ እርምጃ እንደሚከተለው አብራርቷል፡፡

አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ዕሑድ ህዳር 27 ቀን 2002 ዓ.ም የላዕላይ ምክር ቤቱን ስብሰባ በጽ/ቤቱ ጠርቶ ነበር፡፡ የዕለቱ አጀንዳ በላዕላይ ምክር ቤት አባልነት የተመረጡትን ዶ/ር ነጋሦ ጊዳዳን እና አቶ ስዬ አብርሃን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አድርጎ ለመምረጥ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህንን ሂደት የሚቃወመው የእነ ፕሮፌሰር መስፍን ቡድን በአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት በመገኘት ስብሰባው እንዳይካሄድ በፈጠረው አምባጓሮ ከሁለቱም ወገን የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት መድረሱን፣ በተለይም “የአንድነት መርህ ይከበር” ከሚለው ወገን አቶ የሺዋስ አሰፋ የተባሉ ግለሰብ በደረሰባቸው ጉዳት ሆስፒታል መግባታቸውን በአካባቢው የነበሩ እማኞችን ዋቢ ጠቅሶ የዜና ምንጩ ገልጿል፡፡

የዜና ምንጩ ጨምሮ በላከልን መረጃ መሰረት፣ “የአንድነት መርህ ይከበር” የሚለው ቡድን አባላት “እኛ በሌሎች ፓርቲዎች እንደታየው ስንባረር ሌላ ፓርቲ ወደ ማቋቋም አንሄድም፡፡ ዋናው ዓላማችን እንዲህ ዓይነቱን አዲስ ፓርቲ የማቋቋም አባዜ ማቆም ነው” የሚል አቋም ያላቸው ሲሆን፤ በዕለቱ ያደረጉት ግብግብም የፓርቲውን ጽ/ቤት ለመቆጣጠር ነበር ተብሏል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በግጭቱ የፓርቲው ጽ/ቤት በር ከመሰበሩ በስተቀር ጽ/ቤቱን ለመቆጣጠር አለመቻላቸው ታውቋል፡፡

“የአንድነት መርህ ይከበር” ባዮቹ ከያዙት አቋም አኳያ፣ አንድነት ፓርቲ እያደረገው ያለው ከቀውስ ወደ ቀውስ የመሸጋገር ሂደት ማብቂያ የሌለውና ምን አልባትም ወደ ፓርቲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚዛመት ከሆነ ፓርቲው በመጪው ግንቦት ወር በሚካሄደው ምርጫ የሚኖረውን ተሳትፎና በመድረክ ውስጥ የሚኖረውን ሚና አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ ሊከተው ይችላል ሲል የዜና ምንጫችን የላከልን መረጃ አመልክቷል፡፡